**e-mail:** info@eppf.net website: www.eppf.net

# ታላቅ ህዝባዊ የስብሰባ ጥሪ
## በፍራንክፈርት

በግንቦት 1997፤ በኢትዮጵያ በተደረገው ሀገር አቀፍ የህዝብ ምርጫ፤ ቅንጅትን ወክለው በመወዳደር ያሸነፉ የኢትዮጵያ የፓርላማ አባላት የነበሩት፤

**1. አቶ ልዑል ቀስቅስ፤ 2. አቶ አሰፋ ኃይሉ፤**

የህዝባችን ድምፅ በጠራራ ፀሃይ ተቀምቶ ወገናችን ሲጨፈጨፍ፤ሲታሰር፤ ሲሰደድና ንብረቱ ሲቃጠል፤ አምኖ የመረጠን ህዝብ፤ ይህ ሁሉ ግፍና በደል ሲፈጸምበት እጅን አጣጥፎ በወያኔው የአሻንጉሊቶች ፓርላማ መቀመጥ ከአንድ የህዝብ ወኪል የማይጠብቅ መሆኑን በመገንዘብ፤ ለአመታት ብዙ ዜጎች በሃገራችን የተሰዉለትን የዲሞክራሲ ስርአት ምስረታ እውን ለማድረግ፤ በርሃ በማቋረጥ፤ **የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርን፤ (ኢሕአግን)** ከተቀላቀሉ ወራቶችን አስቆጥረዋል።

ኢሕአግን ከተቀላቀሉ ጀምሮ የግንባሩን፤ ድርጅታዊ፤ ሞራላዊና አካላዊ ብቃቱን በማጎልበት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርገዋል። የግንባሩ ከፍተኛ ያመራር አካላት አስፈላጊውን ግምገማና ምክክር በማድረግ ለነኚህ የህዝብ ተወካዮች ውክልና በመስጠት በውጭ ሀገር የሚገኙ ዓባላትና ደጋፊዎችን እንዲያደራጁና ሌሎች ተጓዳኝ ስራዎችንም እንዲያከናውኑ፤ ከፍተኛ ሃላፊነት ሰጥቷቸዋል።

በመሆኑም የግንባሩን፤ ዓላማ፤ ዓርበኛው ለነፃነት በሚከፍለው መስዋእትነት የሚያደረጋቸውን ተግባራዊ ክንዋኔዎች፤ ከኢሕአግ ጎን የተሰለፉብትን ምክንያትና ገጠመኞቻአቸውን፤ ከወቅታዊ የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ሰፋ ያለ ህዝባዊ ውይይት ለመጀመሪይ ጊዜ **በፍራንክፈርት** ያደርጋሉ። በተለይም በውጭ ሀገር ባሉ ደጋፊዎች መሀል ኢሕአግን አስመልክቶ ስለተፈጠረው ብዥታ መረጃን መሰረት ያደረጉ ግልጽ ውይይቶች ስለሚያደርጉ፤
**"ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ"** እንደሚባለው ሁሉ፤ ማየት ማመን ነውና ክቡር ሕይወታቸውን ለነፃነት በመሰዋት ላይ ስላሉት ጀግና አርበኞች፤ የጋራ ግንዛቤና መግባባት እንዲኖረን፡ **ወቅቱና ጊዜው ዛሬ በመሆኑ**፤ በዚህ ታላቅ ሀገራዊ ስብሰባ ላይ እንድትገኙ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባአለን።
በስብሰባው ላይ የኢሕአግ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ አባላትና ጥሪ የተደረገላቸው ታዋቂ ግለሰቦች ይገኛሉ።

| ቀን | ቦታ | ስዓት |
|---|---|---|
| መስከረም (September) 27 ቀን 2008 ዓ.ም ዕለተ - ቅዳሜ | ፍራንክፈርት Frankfurt Am Main Jugendherberger Deutschherrnufer 12 | ከቀኑ 12፡30 ይጀምራል |

በበለጠ ለመረዳት ስ.ቁ. 01744115806 or 015776203683